DISCOVER
ITS BEAUTY

ክፍል 1

# ከብዙው በትንሹ



ዶ/ር ናጂ ኢብራሂም



# ከብዙው በትንሹ

**‘ይህም’...**

- ጥሩ ሀሳብ፣ አዎንታዊ አመለካከት እና ለሌሎች ጥሩ ስሜት እንዲኖረን ያነሳሳናል።
- ሌሎችን ይቅር እንድንል እና ለራሳችን የምንወደውን ለሌሎች እንድንወድ ያስተምረናል።
- በቅንነት ፈገግ እንድንል እና ደስተኛ እና ብሩህ አመለካከት እንዲኖረን ያደርገናል።
- ሌሎችን በትህትና እና በአክብሮት እንድንይዝ ይመራናል።
- ከሰዎች ጋር ጥሩ ስነምግባር እና ጥሩ ባህሪ እንዲኖረን ያዘናል።
- ለእንስሳት፣ ለወፎች እና ለአካባቢው ገር (መልካም) እንድንሆን ያስተምረናል።
- ወላጆቻችንን እና አረጋውያንን እንድናከብር እና እንድንንከባከብ እንዲሁም ለትዳር አጋሮቻችን፣ ለልጆቻችን እና ለቤተሰብ አባላት መልካም እንድንሆን ያስተምረናል።

**ስለ ‘እሱ’ ለማወቅ ጓግተዋል? እስኪ ተጨማሪ ነገር ላካፍልዎ! እንዲሁም...**

- ደካሞችን፣ ድሆችን፣ ችግረኞችን እና አካል ጉዳተኞችን እንድንረዳ፣ እንድንመግብ እና አስፈላጊውን ድጋፍ እንድናደርግላቸው ያበረታታናል።
- ለጋስ፣ በጎ አድራጊ፣ አጋዥ እና ተባባሪ እንድንሆንም ይመራናል።
- በበጎ ፈቃድ ስራ እና በማህበረሰብ አገልግሎት በመሳተፍ አዎንታዊ እንድንሆን ያሳስበናል።
- በጣም ጥሩ የሚባሉ ሰዎች፤ ሌሎችን በጣም የሚጠቅሙ እንደሆኑ ይነግረናል።
- በጣም የተከበሩ ሰዎች ማለት፤ እጅግ በጣም ፈሪሃ እና ፅድቅ ያላቸው፣ ልባቸው የጠራ እና ከምቀኝነት፣ ከጥላቻ እና ከትዕቢት የጸዱ እንደሆኑ ያረጋግጥል።
- እንድናስብ፣ እንድናሰላስል እና እንድናመዛዝን እና እምነታችንን እና ውሳኔዎቻችንን በማስረጃ ላይ እንድንመሰርት ያሳስበናል።



## ሚስጥሩን ይፋ ከማድረጌ በፊት፣ በተጨማሪ የሚከተሉትን ልዘርዝር...

- ሁሉንም ሰዎች ዘራቸውን፣ ቀለማቸውን ወይም ዜግነታቸውን ሳይለይ እኩል መሆናቸውን ያስተምረናል።
- ሁሉንም አይነት አፓርታይድ፣ መደብ ላይ የተመሰረተ መድልዎ እና ዘረኝነትን ይከለክላል።
- ደህንነትን እንድናስጠብቅ፣ ሰላምን እንድናሰፍን እና በምድር ላይ በሰላም እና በስምምነት እንድንኖር ያዘናል።
- በሌሎች ላይ (ድንበርን) እንዳንተላለፍ ወይም ገንዘባቸውን ወይም ንብረታቸውን እንዳንሰርቅ ያስተምረናል።
- ንፁሃንን መግደል ፣ ክህደትን፣ ማታለልን እና ስምምነቶችን(ያለአግባብ) ማፍረስን ይከለክላል።
- በሌሎች ላይ ጥላቻ እንዳይኖረን ያስተምረናል።
- ሌሎች ሰዎችን እንዳንጎዳ፣ እንዳናማ፣ እንዳንሳለቅባቸው እና እንዳንንቃቸው ያስተምረናል።
- ሌሎችን እንዳናታልል፣ እንዳንዋሽ ወይም ስለሌሎች መጥፎ እንዳናስብ ያዘናል።
- ወደ እውነት፣ ፍትህ፣ ታማኝነት፣ ልግስና እና ትህትና ይመራናል።
- ከፈጣሪያችን (ግንኙነት)፣ ከራሳችንና ከሌሎች ጋር ጥሩ ዝምድና እንድንጠብቅም ያስተምረናል።
- የሁሉ ፈጣሪ በሆነው በአላህ (እውነተኛው አምላክ) እንድናምን እና እሱን ብቻ እንድንገዛ ይነግረናል።
- በአደም፣ በኑሕ፣ በኢብራሂም፣ በሙሳ፣ በዒሳ እና በሙሐመድ (የአላህ ሰላም በእነርሱ ላይ ይሁን) በአላህ መልእክተኞች እና ነቢያት ማመንን ያስተምረናል።

**በእርግጥ፣ ወደ መጨረሻው እውነት እና ስኬት፣ እውነተኛ የአእምሮ ሰላም፣ እውነተኛ ደስታ፣ መዳን እና ዘላለም ህይወት ይመራል።**

**አሁን፣ 'እሱ' ምን እንደሆነ ልንገራችሁ ...**



የተቀደሰው መስጂድ፣ መካ፣ ሳውዲ አረቢያ

# እስልምና ነው!

**አእምሮዎች የጨፍን ወይም የጠባብነት ምርኮኞች ከሆኑ፣ የእስልምናን ውበትና እውነተኝነት ፈጽሞ አይገነዘቡም።**

ምናልባትም አንዳንድ አንባቢዎች ስለ እስልምና የተዛባ አመለካከት እና አሉታዊ አስተያየቶችን ይዘዋል።

ምናልባትም በአሸባሪዎች ላይ በማተኮር በመገናኛ ብዙኃን ሲገለጽ ብቻ ያዩት ይሆናል - እነዚያ ሃይማኖታቸው ምንም ቢሆን ከማሸበር ወደኋላ አይሉም።

ምናልባትም ስለ እስልምና ትክክለኛ ካልሆኑ ወይም ከተዛባ ምንጮች አንብበው ወይም ሰምተው ሊሆን ይችላል።

ለማንኛውም ስለ እስልምና የበለጠ አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ

የእስልምናን ውበት እና ቀላልነት የሚያሳየውን ይህን ቡክሌት እና ሌሎች የዚህ **ውበቱን ያግኙ** ተከታታይ ክፍሎች - በቅን ልቦና እጋብዛችኋለሁ ።

በተጨማሪም፣ በዚህ ተከታታይ ውስጥ ስለሚከተሉት ተጨማሪ ዝርዝሮችን ያገኛሉ፡-

- ስለአንዱ እውነተኛ አምላክ፣ ፈጣሪ ስለሆነው አላህ ግልጽ የሆነ ፅንሰ-ሀሳብ
- የአጽናፈ ሰማይ አፈጣጠር
- ስለእኛ አፈጣጠር
- የመኖራችን አላማ
- መንፈሳዊነታችን
- የአምልኮ ጽንሰ-ሐሳብ
- የሕይወት ዓላማ
- እውነተኛ ደስታን እና የመጨረሻውን ደስታን ለማግኘት የሚያስችል መንገድ።
- በሚቀጥለው ህይወት የመጨረሻ መዳረሻችን።

እንዲሁም ስለሚከተሉት ያነባሉ፡-

- የአደም እና የሐዋ ሃይማኖት
- የእስልምና መሠረቶች
- የሰብአዊነት ወሳኝ ጥያቄዎችን መመለስ
- የእርሱ መልካም ስሞች
- የመጨረሻው ወህይ
- የመጨረሻው መልእክተኛ



የነቢዩ መስጂድ፣ መዲና፣ ሳውዲ አረቢያ

# እስልምና ወሳኝ ሰብዓዊ ጥያቄዎችን ይመልሳል

እስልምና ወሳኝ እና ሰብዓዊ ጥያቄዎች በግልፅ ይመልሳል፣ ለምሳሌ፡-

- የመጨረሻው እውነት ምንድን ነው?
- ማን ፈጠረን?
- አምላክ አለን?
- እውነተኛ አምላካችን ማነው?
- የመጨረሻው የአላህ ነቢይ ማን ነው?
- ማንን ነው ማምለክ ያለብን?
- እኛ ማን ነን?
- እዚህ የተገኘንበት ምክንያት ምንድን ነው?
- ከሞትን በኋላ ምንድነው የሚሆነው?
- የሚቀጥለው ህይወት ምን ይመስላል?
- የመጨረሻ መድረሻችን ምንድን ነው - ጀነት ወይስ የጀሃነም (የእሳት)?
- እውነተኛ የአእምሮ ሰላም፣ ስኬት እና እውነተኛ ደስታን ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው?
- የዘላለም ሕይወት ማግኘትስ የምንችለው እንዴት ነው?





ሱልጣን አሕመድ መስጂድ፣ ኢስታንቡል፣ ቱርክ

# ማጠቃለያ

ስለ እስልምና ከትክክለኛ እና ከታማኝ ምንጮች ብዙ ባነበቡ እና በተማሩ ቁጥር፣ የአደም እና የሐዋ እንዲሁም የዘሮቻቸውን እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ እውነተኛ ሃይማኖት መሆኑን የበለጠ ይገነዘባሉ። የእስልምና ሃይማኖት ቀላል፣ ምክንያታዊ፣ ግልጽ፣ ተግባራዊ እና ሁሉን አቀፍ ነው።

የእስልምና ውበት (በነገራቶች) ከማይገደበው፣ የሁሉም ፈጣሪ ከሆነው (አላህ) የመጣ በመሆኑ ውበቱ ወሰን የለውም።

እውነተኛው አምላክ አላህ ውብ በሆነው እና በማይለወጠው ቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

**{ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ።} (5፡3)**

አንድ እና እውነተኛም አምላክ (አላህ) ነቢዩ ሙሀመድ (ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለሰው ዘር በሙሉ (ለአይሁድ፣ ለክርስቲያኖች፣ ለሙስሊሞች፣ ሂንዱዎች፣ ቡዲስቶች፣ አምላክ የለሽ እምነት ተከታዮች፣ አግኖስቲክስ እና ሌሎችም) የተላኩ የመጨረሻው ነቢይ እንደሆኑ ይነግረናል።

አሏህ መመሪያውን እና ቀጥተኛ መንገድን ለሰው ሁሉ ይሰጣል። እርጋታን እና እርካታን እንዲሁም መንፈሳዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሰላምን ማግኘት የምንችልባቸውን ሚስጥሮችን እና ቁልፎችን ይገልጣል።

እስልምና እውነትን በመፈለግ ላይ ፍትሀዊ፣ ጥበበኛ፣ ቅን፣ ታማኝ፣ ተጨባጭ እና አእምሮአችን ክፍት እንዲሆን ያስተምረናል።

**የእስልምናን እውነት እና ውበት ይወቁ!**



ታላቁ አንዋር መስጂድ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# በእስልምና ውስጥ የዋና ዋና ስሞች ፍቺዎች

**አላህ፡-** ማለት ትክክለኛው የአንዱ እውነተኛ አምላክ፣ የፈጣሪ ስም ነው። የሚከተሉትም ከአሏህ ስሞች እና ባህሪያት ጥቂቶቹ ናቸው፡- ጌታ፣ ሩኅሩህ፣ አዛኝ፣ ሉዓላዊው ጌታ (የምሉእ ስልጣን ባለቤት)፣ (ከጉድለቶች ሁሉ) የጠራ፣ (በድርጊቶቹ፣ በስሞቹ እና በባህሪያቱ) መልካም እና ንጹሕ፣ የተባረከ፣ የሰላምና የፍጽምና ምንጭ፣ ፈራጅ (ፍትህን ሰጪ)፣ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን የሚያይ፣ ሁሉን ሰሚ፣ ታላቅ፣ ሁሉን ይቅር ባይ፣ ከሁሉ የላቀ…።

**ነቢዩ ሙሐመድ፡-** (የአሏህ እዝነት በሳቸው ላይ ይውረድ) የብቸኛው እውነተኛ አምላክ የአሏህ የመጨረሻው ነቢይ ናቸው። አላህ ለሰው ልጆች ሁሉ መልእክተኛ አድርጎ ልኳቸዋል። ነቢዩ ሙሐመድ ሰዎች ፈጣሪ የሆነውን አላህን ብቻ እንዲያመልኩ ያዛሉ። ነቢዩ ሙሐመድ በቀሪው የሕይወት ዘመናቸው ይህንን መልእክት እና የእስልምናን አስተምህሮ ለሌሎች አስተላልፈዋል፣ ግሩም አርአያ ሆነዋል፣ እናም ለሰው ልጅ ፍጹም አርአያ ነበሩ።

**የተከበረው ቁርኣን፡-** ለነቢዩ ሙሐመድ የወረደው የአላህ የመጨረሻ ንግግር ነው። ፍፁም በሆነው የፈጣሪ እውቀት ስለፍጥረቱ ይናገራል። እውነቱን ይገልጣል እንዲሁም የሰው ልጅን ወደ እውነት መንገድ ይጋብዛል። ሰዎች ተረድተው ትምህርቶቹን በሥራ ላይ ለማዋል ጥረት ሲያደርጉ፤ በማስተማር ወደ ከፍተኛ መንፈሳዊ፣ ሥነ-ምግባራዊ፣ ጥበባዊ እና ማህበራዊ ደረጃ ያደርሳቸዋል።

**እስልምና፡-** እውነተኛ አምላክ የሆነውን አላህ (በብቸኝነት) መገዛት ማለት ነው። እስልምና የደስታ፣ የእርካታ እና የዘላለማዊ ሕይወት መግቢያ በር፤ እውነተኛ አምላክ በሆነው አላህ እና በመጨረሻው ነብይ ነቢዩ ሙሐመድ በማመን እንደሆነ እንዲሁም ይህንን የምስክርነት ቃል መናገር እንደሆነ እንዲህ ሲል ያስተምረናል፡- **"ከአላህ በስተቀር በእውነት እና በብቸኝነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።"**



የለንደን ማዕከላዊ መስጂድ፣ ዩናይትድ ኪንግደም

እስልምናም በአሏህ እና በነቢያቱ ማመን ብቻ የአእምሮ ሰላም፣ ደስታ እና መዳን ለማግኘት በቂ እንዳልሆነ ይነግረናል! የአሏህን ፈቃድ መፈፀም ያለብን ፈጣሪን አሏህን ብቻ በመታዘዝ እና (በብቸኝነት) በማምለክ ነው።

**ሙስሊም፡-** ለፈጣሪው አላህ የተገዛ (እራሱን የሰጠ) ሰው ማለት ነው። ሙስሊሞች በአላህ ላይ እምነት አላቸው፣ መልካም ስራዎችንም ይሰራሉ። ነቢዩ ሙሐመድ፣ ነቢዩሏህ ዒሳ እና ሁሉም ነቢያት ያስተማሩትን እና የታዘዙትን ትእዛዛት ያከብራሉ፣ ለምሳሌ በአንድ እውነተኛ አምላክ ማመን፣ መጸለይ፣ መስገድ እና መንበርከክ፣ ጾም እና ምጽዋትን በመስጠት ለወደፊቱ ዕቅዶቻችን “አሏህ ከፈቀደ (ኢንሻ አሏህ)” ይላሉ እንዲሁም የነቢዩሏህ ዒሳን እና የነቢያትን ሰላምታ በመጠቀም “ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን ( አሰላሙ ዓለይኩም ) ይላሉ።

**መስጂድ፡-** ሙስሊሞች በዋናነት ለሶላት (ለሰግደት) እና ለአምልኮ የሚጠቀሙበት ንፁህ የስግደት ቦታን ያመለክታል። በተጨማሪም መስጂድ ጸጥ ያለ እና ሰላም የሰፈነበት እንዲሁም አላህን (ፈጣሪን) ለማውሳት እና እሱን ለመማፀን፣ የተከበረውን ቁርኣን ለመቅራት፣ ስለ እስልምና አስተምህሮ እና የነቢዩ ሙሐመድን መመሪያዎች ለመማር የሚያገለግል ነው። ለህብረተሰቡ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ በጎ አድራጎት እና ትምህርታዊ አገልግሎቶችንም ይሰጣል።



አላህ በአረብኛ



አላህን (እውነተኛውን አምላክ) የሚማፀን ሙስሊም



የተከበረው ቁርኣን



ሙሐመድ በአረብኛ



አል-አቅሳ መስጂድ፣ አል-ቁድስ፣ ፍልስጤም

# የማወቅ ጉጉት አልዎት?

የማወቅ ጉጉት ካሎት እና ስለ እስልምና ተጨማሪ መረጃ እና ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ እባክዎን ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ፡-

**www.discoveritsbeauty.com**

## የውበቱን ያግኙ ተከታታይ ቡክሌቶች፡-

1. ከብዙው በትንሹ
2. የአደም እና የሐዋ ሃይማኖት
3. የእስልምና መሠረቶች
4. የሰብአዊነት ወሳኝ ጥያቄዎችን መመለስ
5. የእርሱ መልካም ስሞች
6. የመጨረሻው ወህይ
7. የመጨረሻው መልእክተኛ

## ጠቃሚ ኢስላማዊ ድረ-ገጾች፡-

**http://www.allahsquran.com**

**http://www.quranexplorer.com**

**http://www.islamhouse.com**

**http://www.edialogue.org**

**http://www.islamreligion.com**

**http://www.newmuslimguide.com**

**http://www.guidetoislam.com/en/**

# የእምነት ምስክርነት (የእስልምና መግቢያ በር)

“ከአላህ በስተቀር በእውነት እና በብቸኝነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።”

በአረብኛ እንዲህ ይነበባል፡-





ሲነበብ ይህን ይመስላል፡-

**አሽ-ሀዱ አላ ኢላሀ ኢለ ሏህ**

**ወ አሽ-ሀዱ አነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ**

ይህ አንድ ሰው እስልምናን ለመቀበል በአፉ መናገር ያለበት የእምነት ምስክርነት ነው። የእስልምናን እውነተኛነት፣ ውበት እና ቀላልነት አንድ ላይ ይዟል።







DISCOVER
ITS BEAUTY

WWW.DISCOVERITSBEAUTY.COM

ይቃኙት

GLOBAL ACADEMY FOR TRANSLATION AND EDUCATION (GATE)
LONDON | THE UNITED KINGDOM

በAL-ANDALUS GROUP LTD የተተረጎመ
www.alandalusgroup.org

كتاب رأس الجبل الجليدي باللغة الأمهرية